# የእግዚአብሔር እውነት
# የመሠረተችውን፡ የኢትዮጵያዊነት ሥርዓት፣
# ሊያጠፋ ሲቃትት የኖረው የዲያብሎስ ሓሰት፣
# በድቡሽት ላይ የሠራውን የስሕተት ሓውልት፣
# በራሱ ሲያፈራርሰው፡ በእውን ማየትና መስማት፤
# ምን ይደንቅ! ምን ይገርም! እንዴትስ ያስደስት?!

---

የዓውደ ዓመት መግቢያና መጀመሪያ የኾነው፡ መስከረም ፩ (አንድ) ቀን፡ በጥንታዊው የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖታችን ሥርዓት፡ በባሕረ-ሓሳብ፣ ማለትም፡ በቀን አቈጣጠር የስሌት ትንታኔ መሠረት፡ ለየዘመኑ፡ የዓመት ሽግግር፡ መደብ፥ እንዲሁም፡ ለመዓልትና ለሌሊት፥ ለዕለትና ለወርኀ፥ ለአጽዋማትና ለበዓላትም ቅመራ፡ መነሻ ኾኖ፡ እስከዛሬ፡ ለ፯ሺ፭፻፭ (ሰባት ሽህ አምስት መቶ አምስት) ዓመታት ጸንቶ፡ ኢትዮጵያውያንንና ኢትዮጵያውያትን ሲያገለግላቸው ኖርዋል።

ይኸው፡ መስከረም ፩ ቀን፡ ዘመነ ፍዳና ሕገ ኦሪት አልፈው፡ ገነታዊና መንግሥተ-ሰማያዊ የኾነውን፡ የትንሣኤንና የሰንበትን ዘለዓለማዊ ሕይወትን ያስገኘውን፡ ዓመተ ምሕረትንና ዘመነ ምሕረትን፡ ለፍጥረተ-ዓለሙ፡ ለአንዴና ለመቼውም ጊዜ፡ በመለኮታዊው የትስብእት ደም ዐትመውና አረጋግጠው ያበረከቱት፡ ኢትዮጵያዊቷ የአምላክ እናት፡ ቅድስት ድንግል ማርያምና ልጇ ወልደ-እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለዱበት ዕለት መኾኑንም ይታወቃል።

እናንተ፡ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት የኢትዮጵያ ልጆች ኹሉ፡ ይህንኑ የእግዚአብሔር እውነታ አውቃችሁትና አምናችሁበት፥ ተቀብላችሁትና ፈጽማችሁት፡ እነሆ፡ በየዓመቱ ስታከብሩት ትታያላችሁ።

ይኹን እንጂ፡ "ክርስቲያን ነኝ!" የሚለው ዓለም፣ ማለትም፡ ኦርቶዶክሱም፥ ካቶሊኩም፥ ፕሮቴስታንቱም፡ "ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደው፡ የአረማውያን ጣኦታት በዓል ማክበሪያ በነበረው፡ በታኅሣሥ ሃያዎቹ ቀኖች ውስጥ ስለኾነ፡ የልደቱ ቀን፡ ሊከበር የሚገባው፡ በዚህ ወርና ቀናት ክልል ነው!" ብሎ አምኖና ወስኖ፡ በዚሁ ጊዜ ውስጥ ሲያከብረው እንደኖር፥ አኹንም፡ በዚሁ መልክ እያከበረው እንደሚገኝ፡ ድርጊቱ፡ ይኸው በገሃድ ይታያል።

"የማታ ማታ! እውነት ትረታ!" ነውና፡ ዛሬ ግን፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ጥበብና ኃይል፡ ይኸው ክርስቲያኑ ዓለም፡ ቋሚ ባህል አድርጎት የኖረበት፡ የዚሁ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ የልደቱ ቀንና የዓመታቱ ስሌት የተሳሳተ መኾኑን፥ እውነተኛውና ትክክለኛው፡ የልደቱ ቀንና የዓመቱ አቈጣጠርም፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊው ሃይማኖት አጽንቶት የኖረው፡ መስከረም ፩ (አንድ) ቀንና የያዝነው፡ ፳፻፭ኛው (ሃያ መቶ አምስተኛው፣ ወይም፡ ኹለት ሺህ አምስተኛው) ዓመተ-ምሕረት መኾኑን፡ ይኸው አኹን፡ በትክክል ተረድቶ፡ እውነታውን፡ ራሱ፡ በራሱ፡ ይፋ አውጥቶታል።

ይህንኑ እውነት፡ እናንተም፡ ትገነዘቡት ዘንድ፡ ሌላውም፡ ያውቀው ዘንድ፡ የዜናውና የመልእክቱ ምንጮች የኾኑትን መገናኛ ዐውታሮች፡ በመጻሕፍቶቻችንና በጎዋ ሰሌዳችን ላይ በሠፈሩት መልእክቶች ውስጥ የተገለጹ አንዳንድ ተመሳሳይ ቍም-ነገሮችን ከያዙ ጋር፡ ጥቂቶቹን፡ ከዚህ በታች አቅርበንላችኋል። የመቀመሪያችሁን መቈጣጠሪያ ተጭናችሁ፡ እያንዳንዱን መገናኛ ዐውታር እየከፈታችሁ በመመልከት፡ የኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖታችን የኾነው ቅዱሱ ኪዳን፡ ያስገኘውን ተአምራዊ ድንቅ ሥራ እያስተዋላችሁ፡ በአንክሮና በተዘክሮ፥ በሓሤትም ተመሠጡበት!

http://www.telegraph.co.uk/news/religion/the-pope/9693576/Jesus-was-born-years-earlier-than-thought-claims-Pope.html

http://www.truthortradition.com/modules.php?name=News&file=article&sid=467

http://bytheword.com/birth

http://www.godlikeproductions.com/forum1/message478994/pg1

http://www.cortright.org/birth.htm

http://www.youtube.com/watch?v=QOaLoKIhsi8

NASA thinks the birth of Hurricane is Ethiopia

http://www.youtube.com/watch?v=mm4m5f9ziA4&feature=share